# የተቃርኖ ርእዮተ-አለም፤ የመበልፀግ ተስፋና የሰላም መናጋት

ስሜነህ 02-06-18

ሃገሪቱን ቀውስ ውስጥ የከተቱ ጉዳዮችን ተከትሎ የኢትዮጵያ ህዝቦች አብዮታዊ ዴሞክራሲያዊ ግንባር /ኢህአዴግ/ የስራ አስፈፃሚ ኮሚቴ ከታህሳስ 3 ቀን ጀምሮ አገራችን የምትገኝበትን ወቅታዊ ሁኔታ መነሻ በማድረግ 17 ቀናት የፈጀ ሰፊና ዝርዝር *የሁኔታዎች ግምገማ* ማካሄዱ ይታወሳል፡፡ ስራ አስፈፃሚ ኮሚቴው በዚህ ስብሰባ ቀደም ሲል የተጀመረው የመታደስ ሂደትና የተደረሰበትን ውሳኔ እንዲሁም በአገራችን የሚታዩ የቆዩና ወቅታዊ ችግሮችን ከነዝርዝር መገለጫቸው በመለየት በመንስኤና መፍትሄዎቻቸው ላይ መክሮ የሃሳብ አንድነትና መተማመን መፍጠሩን አመልክቷል፡፡

የሥራ አስፈፃሚ ኮሚቴ ባደረገው በዚሁ ግምገማ በየደረጃው ባሉ የአመራር እርከኖች በተለይ ደግሞ በከፍተኛው አመራር ደረጃ የውስጠ ድርጅት ዴሞክራሲ እጦት ስር እየሰደደ መምጣቱ የቀውሱ ዋነኛው ምክንያት እንደሆነ ተጠቅሷል፡፡ ይህም ሐሳብ በነፃነት የሚንሸራሸርባቸውን የመታገያ መድረኮች የሚገድብና የሚያጠብ፤ ስለዚም ደግሞ በአመራሩ ውስጥ የአመለካከትና የተግባር አንድነትና ጥራት እንዳይፈጠር መሰናክል እንዲሆን በማስቻሉ የቀውስ ምክንያት እንደሚሆን አያጠያይቅም፡፡ ይህ ችግር በዋነኛነት በድርጅቱ ከፍተኛ አመራር ደረጃ ከታየው የተዛባ የስልጣን አተያይና አጠቃቀም ጋር ተያይዞ የተከተሰተ መሆኑም ተገልጿል። ችግሩ የድርጅቱ አይነተኛ መለያ የሆነውን ዴሞክራስያዊነት በማዳካም ሳይወሰን ስልጣን የህዝብ መገልገያ እንዲሆን የተጀመረውን መልካም ጉዞ ለአደጋ አጋልጧል።

ዴሞክራሲ እየጠበበ አድርባይነት በመስፋፋቱ ምክንያት በግልጽነትና በመርህ ላይ ተመስርቶ ከመተጋገል ይልቅ መርህ አልባ ግንኙትና አካሄድን ማስፈን የተለመደ ስልት መሆኑም ሌላኛው የቀውሱ ምክንያት

ነው፡፡ ልማታዊ መንግስትታት በጠንካራ ዲስፒሊንና የሃሳብና የተግባር አንድነት የሚታወቁ ሆኖ እያለ ተገቢ ባልሆኑ ጥቅሞች ላይ የተመሰረቱት የቡድን ትስስሮች መንግስትና ድርጅቱ ተልእኳቸውን በብቃት እንዳይፈፅሙ ከፍተኛ መሰናክል ሆኖ እንደቆየ ስራ አስፈፃሚ ኮሚቴው አረጋግጧል፡፡

እንደሚታወቀው በአገራችን የሚገነባው ፌዴራላዊ ስርዓት መላ የአገራችን ብሄር ብሄረሰቦች ለዘመናት ያካሄዱት ትግል ውጤት ነው፡፡ አዲሲቱ ኢትዮጵያ ከየትኛውም ህብረብሄራዊ አገር የምትለየው ብዝሃነትን በማወቅና በማክበር ነው፡፡ ለ26 አመታት የተገነባው ፌዴራላዊ ዴሞክራሲያዊ ስርዓት የቋንቋ፣ የባህልና የታሪክ እኩልነትን አረጋግጧል፡፡ የአገራችን ብሄር ብሄረሰቦች ራሳቸውን በራሳቸው ካልሆነ በቀር በሌላ የማይተዳደሩበትን ሁኔታ ፈጥሯል፡፡ ፌዴራላዊ አስተዳደራዊ ስርአቱ በእኩልነትና በመተሳሰብ የሚሳተፉበትን ሁኔታም አመቻችቷል፡፡ በዚህ የተነሳ ስርዓቱ ለበላይነትና የበታችነት የማይመች ሆኖ ተዋቅሯል፡፡ በተግባርም እኩልነት እንጂ የባላይነትም ሆነ የበታችነት የማይፈጠርበት ስርዓት ተገንብቷል፡፡ ይህንን መሰረታዊ መርሆ የሚነካ ማንኛውም ዝንባሌ የበላይነትን በዘላቂነት ሊፈጥር የማይችልና ከመናቆርና ቀውስ ከመፍጠር የዘለለ ሌላ ምንም አይነት ውጤት ሊያስገኝ አይችልም፡፡

ይህ እንደተጠበቀ ሆኖ በአንድ ወይም በሌላ ብሔር ህዝብና ድርጅት ስም እየማሉና እየተገዘቱ ጥገኛ ፍላጎታቸውን ለማርካት የሚንቀሳቀሱ ወገኖችን እንቅስቀሴ አሁንም የቀውስ ምክንያት እንደሆነ ቀጥሏል፡፡ ሁሉም ብሔራዊ ድርጅቶች በሚያስተዳድሩት ክልል ውስጥ ያሉ ጥገኞችን ያለልዩነትና ማመንታት መታገል እንዳለባቸው ስምምነት ላይ ቢደረስም፤ ለስምምነቱ ተገዢ ያልሆኑ አመራሮች አሁንም ቀውሱን በማስቀጠል ሂደት ላይ ስለመሆናቸው በወልዲያ፣ ቆቦና ሃራ ላይ ለተፈጸሙት ግጭቶች ምክንያቱ የአመራር ችግር ነው የሚለው የአማራ ክልል ርእሰ መስተዳድር መግለጫ ሁነኛ ማጠየቂያ ነው፡፡

ሥራ አስፈፃሚው በድርጅቱ የዴሞክራሲ መጥበብ እዛው በዛው የውሳኔዎችን በታማኝነትና በቁርጠኝነት

የመፈፀም ዲሲፒሊንን እያላላ እንደመጣ ማረጋገጡም ይታወሳል፡፡ በዚህ የተነሳ በድርጅትና በመንግስት ቋሚ መመሪያዎች በመገዛት መፈፀም የነበረባቸው ተግባራትና መሰጠት የነበረባቸው የእለት ተለት ውሳኔዎች እየቀሩ በብዙ የመንግስት መ/ቤቶች ህዝብ የሚጠብቃቸው አገልግሎቶች የማይሟሉበት ሁኔታ መፈጠሩም የቀውስ ምክንያት መሆኑንም አመልክቷል፡፡ ያም ሆኖ ግን በግምገማው የተሰጡ ውሳኔዎችን አሁንም ከስር ከስር መፈጸም ያልተቻለ መሆኑ የቀውሱ አንዱ ምክንያት መሆኑንም ብዙዎች ሲናገሩ እየተደመጠ ይገኛል።

በጸሃፊው እምነት የዚህ ችግር መነሾ የውሳኔ አሰጣጡ ሳይሆን የስራ አስፈጻሚው መግለጫ ነው። ስራ አስፈጻሚው ባደረገው የግምገማ ውጤት አግባብ ከላይ የተመለከቱ እና ቀጥለው የሚመጡ ውሳኔዎችን ቢያሳልፍም፤ ግን ደግሞ ሁሉንም በአንዴ ሊፈጽም የሚችልበት አመክንዮም ሆነ አቅም አይኖረውም። ይህ እየታወቀ የስራ አስፈጻሚ ኮሚቴው መግለጫ ድርጅታዊ እና መንግስታዊ የአፈጻጸም ቅደም ተከተሎችን ያላብራራ ከመሆኑ ጋር ተያይዞ በህዝቡ ዘንድ የተፈጠረው ብዥታ *ዛሬም የተገባልን ቃል ተበልቷል* በሚል የግጭት ምክንያት ለመሆን በቅቷል። መፍትሄውን በትክክል ለይቶ ሲያበቃ በመግለጫ እጥረት የህዝቡን የግንዛቤ ልህቀት ባላገናዘበ እና በድርጅታዊ ቋንቋ በታጀለ አግባብ የወጣው መግለጫ እንደገና የግጭት ምክንያት ሲሆን ሁለቴ እንደመውደቅ ነው።

ለሰላማችን መታወክ አመራሩ የራሱን አስተዋጽኦ አበርክቷል የሚባልባቸው በርካታ ማሳያዎች አሉ። በአጠቃላይ በድርጅቱ በተለይም ደግሞ በሥራ አስፈፃሚው ውስጥ የታየው የውስጠ ድርጅት ዴሞክራሲ ችግር ባለቤቱ አመራሩ ነው። አደጋው በድርጅቱ ውስጥ ብቻ ታጥሮ እንዳይቀር በህዝብና በአባላቱ ውስጥም ጭምር ያሰረጸው አመራሩ ነው፡፡ የአመራሩ አስተዋጽኦ የህዝብ መብትን በማክበርና ተገቢውን ህጋዊ አገልግሎት የመስጠት ግዴታን ባለመወጣት ጭምር የሚገለፅ ነበር፡፡ ከዚያም አልፎ ዴሞክራሲያችንን ማስፋትና ማጠናከር ሲገባ በተለያዩ መንገዶች የማጥበብ አዝማሚያም የተስተዋለው

ከሁሉ በላይ በአመራሩ ዘንድ ነው የሚለው የብዙዎች አስተያየት ስለትክክለኛነቱ ሚዛን እየደፋ ያለ ይመስላል፡፡

ህገ መንግስታዊ ስርአቱ ልዩ ልዩ ጥቅሞችና ፍላጎቶች እንዲሁም በእነዚህ ላይ የተመሰረቱ ልዩነቶች በዴሞክራሲያዊ፣ ህጋዊና ሰላማዊ መንገድ እንዲስተናገዱ በቂና አስተማማኝ እድል ከፍቶ እያለ አመራሩ ዴሞክራሲውን የማስፋት ግዴታውን ባለመወጣቱ ችግሮችና ልዩነቶች በግጭት መንገድ የሚፈቱበት ሁነታ እንዲፈጠር አስተዋፅኦ አድርጓል፤ ይህም ለሰላማችን መታወክ የበኩሉን አስተዋፅኦ አድርጓል የሚሉ ድምፆች በስፋት መደመጣቸው በቀላሉ የሚታይ ጉዳይ አይደለም፡፡

በክልሎችም ሆነ በክልሎች መካከል በልዩ ልዩ ሰበቦች የሚከሰተው የሰላም መደፍረስ ለዜጎቻችን አሳዛኝ ሞት መበራከትና መቁሰል እንዲሁም ከባድ መፈናቀል ምክንያት ሆኗል፡፡ በተጨማሪም ከፍተኛ የንብረት ውድመትንና የኢኮኖሚ እንቅስቃሴ መገታትን አስከትሏል፡፡ ይህ ለረጅም አመታት በሰላም በኖረችው አገር ውስጥ የስጋት መንፈስና ጭንቀት ፈጥሯል፡፡ በየቦታው እየተነሱ ያሉ ግጭቶች ከሰው ሞትና ከንብረት ውድመት በዘለለ የሃገራዊ ሕልውናችን ለአደጋና ሕዝቡን ለጥፋት ቋፍ ያደረሱበት ሁኔታ ከመኖሩ በላይ ለውጭ ጥቃት ተጋላጭነታችንን የመጨመር ውጤት አስከትለዋል፡፡ ይህም በአጭር ቃል የመበልፀግ ተስፋና የሃገራዊ ሰላም መናጋት የተፋጠጡበት ሁኔታ ላይ እንድንገኝ አድርጎናል፡፡

ከዚህ በመነሳት ስራአስፈፃሚ ኮሚቴው ህገመንግስታዊ ዴሞክራሲያችንን በታማኝነት ተግባራዊ ማድረግ ብቻ ሳይሆን መድረኩ የሚጠይቀውን ሁኔታ መነሻ በማድረግም ማስፋትና የግጭት መንስኤዎችን መቅረፍ፤ እንዲሁም የአገራችንን ሰላም ወደተለመደው አስተማማኝ ሁኔታ በአጭር ጊዜ መመለስ እንደሚገባ ወስኗል፡፡ የውሳኔው ቅደም ተከተል በመግለጫው ባለመብራራቱ ደግሞ ዳግም የጥፋት ዘመቻ እንዲጀመር ምክንያት ሆኗል። በዚህም ዛሬም ሃገራችን የመበልፀግ ተስፋና የሃገራዊ ሰላም መናጋት

የተፋጠጡበት ሁኔታ ውስጥ እንድትቆይ ምክንያት ሆኗል።

በሃገራችን የሚገነባው ህገመንግስትታዊ ዴሞክራሲያዊ ስርዓት በፍላጎትና ጥቅሞች ብዝሃነት ላይ የተመሰረተ ነው፡፡ ከዚህ በመነሳት የመድብለ ፓርቲ ዴሞክራሲያዊ ሥርዓት ግንባታ በድርጅታችንና በመንግስት መሪነት ለ26 አመታት የቀጠለ ቢሆንም ከቅርብ አመታት ወዲህ የአስተሳሰብ ብዝሃነት በአግባቡ እንዲገለፅ የሚያደርግ ተጨባጭ ሁኔታ እየተዳከመ እንዲመጣም ምክንያት የሆነው አመራሩ ነው፡፡ ይህንን ችግር በጊዜና በአግባቡ ተገንዝቦ ማስተካከል የሚገባው ገዥው ፓርቲ ተገቢውን ህጋዊ እርምጃ በመውሰድ ረገድ ያሳየው ዳተኝነት የመድብለ ፓርቲ ስርግቱን ችግር እንዲገጥመው አላደረገም ማለት አይቻልም፤ ለምን ቢሉ፣  ከዚህም በስተጀርባ ቢሆን የሚገኘው ሌላ ሳይሆን ያው አመራሩ ነውና ነው።

ለዴሞክራሲ ሥርዓት ግንባታ ሁነኛ ድርሻ ካላቸው ተቋማት መካከል የሃገራችን ሚዲያና ፕሬስ በሚገባው ደረጃ ነፃነታቸው ተጠብቆ የህዝብ ዓይንና ጆሮ ሆነው ያገለግሉ ዘንድ የተደረገው እንቅስቃሴ የሚፈለገውን ውጤት እንዳላመጣ ሥራ አስፈፃሚ ኮሚቴው በግምገማው መመልከቱን ይፋ አድርጓል፡፡ በዚህ ረገድ የታየው ዘገምተኛ ዕድገት እንደተጠበቀ ሆኖ ከቅርብ ጊዜያት ወዲህ በክልልም ይሁን በፌዴራል ያሉ የህዝብ የሚዲያ አውታሮች ሕግና ሥርዓትን ጠብቀው የማይሠሩበት ሁኔታ እያመዘነ የህዝቡን ሰላምና አብሮ የመኖር ገንቢ ባህል የሚሸረሽሩ ሰበካዎች የሚሰጥባቸው፤ ብሎም ህዝብን ከህዝብ ጋር የሚያጋጩ አጥፊ እንቅስቃሴዎች የሚካሄድባቸው እየሆኑ ለመምጣታቸውም ከጀርባው የሚገኙት አመራሮች ስለመሆናቸው ብሮድካስት ባለስልጣን ሰሞኑን ካዘጋጀው መድረክ በላይ አስረጅ መጥቀስ አይጠበቅብንም። በዚህም ሃገራችን በመበልፀግ ተስፋና የሃገራዊ ሰላም መናጋት የተፋጠጡባት ሁኔታ ውስጥ እንድትቆይ ሆኗል። ስለሆነም አመራሩን የተመለከተ ፖለቲካዊና መንግስታዊ አስቸኳይ ውሳኔዎች የዚህችን ሃገር እጣ ፈንታ የሚወስኑልን ይሆናሉ።